# <u>አትሰቀል ይቅር</u> !! እና <u>ተጠየቅ ልጠየቅ</u> !!

( አሥራደው ከፈረንሳይ )



በገባለት ቃሉ - አባትህ ለእኛ አባት፤
አንተ ለኛ ሞተህ - ልንድን ከሃጢያት፤
እኛን አድናለሁ - ብለህ ከመከራ፤
መስቀል ተሸክመህ - አትውጣ ተራራ።

በጨካኞች ጅራፍ - አይገረፍ ጀርባህ፤
ምስማር አይቸንከር - በጅና በግሮችህ፤
በጦር አይወጋ - አይበሳ ጎንህ፤
አትጠጣ ፍጹም - የሃሞት መራራ፤
አድናለሁ ብለህ - እኛን ከመከራ፤
መከራህ አይብዛ - መከራችን ላይቀር፤
ተንገላተህ አትሙት - አትሰቀል! ይቅር።

ተከባብሮ መኖር - አብሮ መብላት ቀርቶ፤
ጥላቻ፤ ጭካኔ - መከራ በርክቶ፤
ወንድማማችነት - ፍቅር መተባበር፤
አንድነት፤ ነፃነት - ፍጹም ጠፍተው ካገር፤
መቻቻል፤ ደግነት- ከሃገር ተሰደው፤
ግፍ በደል በርክቶ - ሞልቶ ፈሶ ጽዋው፤

ሰው ሆነን ሰው ካልሆን - ተፈጥረን ባምሳልህ፤

ከሰማየ ሰማይ - ወርደህ ከዙፋንህ፤

አፈር ለባሽ ገላ - ከንቱ ሥጋ ለብሰህ፤

አትሰቀል በቃ! - እኛን ላድን ብለህ ።

ይልቅስ ከሰሙህ_ እንዲህ ምከራቸው.........!

እንደዚህ በላቸው_ ስልጣን ላዋስካቸው.... !

ስልጣን ተገን አርጎ - ቀምቶ የበላ፤

ለሥጋው አድልቶ - ወገኑን ያጉላላ፤

ዘረኝነት አርሶ - ቂም በቀል የዘራ፤

የሚያበዛ ትዕቢት - ሰው የሚያስፈራራ፤

ውሸት ያመረተ - በደል የከመረ፤

በግፍ የገደለ - ወህኒ ቤት ያጎረ፤

ጥላቻን አንግሶ - ፍቅርን ያኮሰሰ፤

ወንድሙን የገፋ - በደል ያነገሰ፤

ቁጣዬን አብዝቶ - መከራውን ያጭዳል፤

ሕዝቤን አታጉላሉ - ከንግዲህ ይበቃል !

ብለህ ንገራቸው.........!

ስልጣን ላዋስካቸው......... !

ልቦና ቢገዙ_ ድንገት ቢመለሱ_ ወደ ሕሊናቸው ።

ግን !

የሕዝብህን ጩኸት - እየሰማ ጆሮህ፤

ስቃይ መከራውን - እያየኸው ባ'ይንህ

ሲካድ ሰብዕናው - ፈጥረኸው ባምሳልህ፤

ዝምታህ ከበዛ - ከዘገየ ፍርድህ፤

ኤሎሄ ! ኤሎሄ ! ላማ ሰበቅታኒ - ላ'ባትህ ልናገር፤

ቁም ስቅልህ ይብቃ!_ እኛ አልዳንምና - አትሰቀል ይቅር!!

# ተጠየቅ ልጠየቅ !

( አሥራደው ከፈረንሳይ )



« በአገር በሃይማኖት፤ በሚስት የለም ዋዛ !

በአሞሌ አይለወጥ፤ በአራጣ አይገዛ !! »

ብሎ የዘመተው ፤

በአድዋ በማይጨው ፤

ለአገር ለነፃነት ሕይወቱን የሰዋው ፤

ለኛ ሲል የሞተው ፤

ድንበር ያስከበረ - ባጥንቱ ቸንክሮ ፤

ባ'ንድነት ያሰረ - በጅማቱ አከርሮ ፤

ቆዳው ተፈቅፍቆ - ብራና ተሌጦ ፤

ታሪኩ የተጣፈ - በደም ተበጥብጦ ፤

ሰንደቅ የሰቀለው - ባጥንቱ ሰክቶ፤

በሥጋ ወ ደሙ - በቃል ኪዳን ጠንቶ ፤

ለሰጠን አደራ - ለቃል ኪዳናችን ፤

ዛሬ ቢጠይቀን፤

ምንድነው መልሳችን ?!

በአሞሌ ለሸጥነው - ለነፃነታችን ፤

ለተቸበቸበው - ለባዕድ መሬታችን ፤

ለተሸራረፈው - ያገር ድንበራችን ፤

ለተሸረሸረው - ጥኑው ዕምነታችን ፤

ለ'ኛ ሲል የሞተው ፤

በአድዋ በማይጨው ፤

ዛሬ ቢጠይቀን ፤

ምንድነው መልሳችን ?!

ለቃል ኪዳናችን - መፍረስ ወይ መጠበቅ ፤

መልሳችን ምንድነው ?_ ተጠየቅ ልጠየቅ ?!

ቢጠይቅ ታሪኩን ፤

ቢያነሳ አደራውን ፤

በደም የተጣፈ - ያ'ባት ኑዛዜውን ፤

ምንድነው መልሳችን ?!

ለሰጡን አደራ - ማረጋገጫችን ፤

ለ'ኛነት መግለጫ - የ'ኛነት ቃላችን ?!

ለቃል ኪዳናችን - መፍረስ ወይ መጠበቅ ፤

መልሳችን ምንድነው ?_ ተጠየቅ ልጠየቅ ?!

መልስ የሚሻ ለሁላችን የቀረበ ጥያቄ !!

የመጀሪያው: አምላክ ጆሮውን ቢያውሰን፤ ጨንቁሬ የላኩለት ደብዳቤ ሲሆን፤
ሁለተኛው ደግሞ፤ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፤ ድንገት ቢያዳምጡኝ ብዬ፤ ያቀረብኩት ጥያቄ ነው ፡፡

ቀደም ብሎ: በተለያዩ ጊዜያት፤ ከተጣፉት: በጣጥፎቼ፤ መሃል የተወሰዱ ፡፡